የሰ/መ/ቁ. 16195

ሚያዚያ 11 ቀን 1999 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

**አመልካች፡-** የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት

**ተጠሪዎች፡-** እነ ልዕልት ተናኘወርቅ ኃ/ሥላሴ

*የቤት አበል ክፍያ - የተወረሰ ቤት - የጠቅላይ ሚ/ር ስልጣን - የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 74(4) - የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁ. 4/87 አንቀጽ 11/1/ - አዋጅ ቁ. 47/67 አንቀጽ 21(2)*

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ቤት የተወረሰባቸው በመሆኑ አበል ሊከፈላቸው ይገባል ሲል የሰጠውን ውሣኔ በማፅናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>**ውሣኔ፡ -**</u> የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚኒስቴር መ/ቤቶችን በበላይነት የመምራትና ስራዎቻቸውንም የመቆጣጠር ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡
2. ሚኒስቴር መ/ቤቶች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የፈፀሙትን ስህተት ማረምና ማስተካከል በጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው፡፡





**ዳኞች፡-** 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ
2. አቶ አሰግድ ጋሻው
3. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
4. ወ/ት ሂሩት መለሠ
5. አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

**አመልካች፡-** የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት - ነ/ፈጅ ሂሩት አስራት ቀረቡ፡፡

**መልስ ሰጭ፡-** እነ ልዕልት ተናኘወርቅ ኃ/ሥላሴ /6 ሠዎች/ - ጠበቃ አቶ ብስራት ሐመልማል ቀረቡ፡፡

<u>**ፍ ር ድ**</u>

ለሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡

ተጠሪዎች ለዚህ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ መንግስት የግል መኖሪያ ቤቶቻቸውንና አከራይተው የነበሩትን ሌሎች ቤቶች ወርሶ እያስተዳደረ በመሆኑና ምንም ገቢ ስላልነበራቸው አበል እንዲከፈላቸው ለሥራና ከተማ ሚ/ር አመልክተው እንዲከፈላቸው የተወሰነ ቢሆንም ተጠሪ አበሉን ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከ1/12/67 - 30/8/87 ያለው ውዝፍ አበልና ወደፊት ያለው አበልም ለዘለቄታው እንዲከፍል እንዲወሠንበት ጠይቀዋል፡፡ ጉዳዩን ያየው ፍ/ቤትም ውዝፍ አበሉ እንዲከፈልና ከክሱ በኂላ ያለው ግን ዳኝነት ያልተከፈለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱን ውሣኔ አፅንቷል፡፡

የአሁን የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታም የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር የሰጠው ውሣኔ በጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ ተሽሯል፣ ተጠሪዎች እስር ቤት በነበሩበት ጊዜ መንግስት ወጪ እያደረገ ያኖራቸው በመሆኑ ተጠሪዎች ውጭ አገር ነዋሪዎች በመሆናቸው ከቤት ኪራይ በቀር ሌላ ገቢ እንደሌላቸው ሣይጣራና ሣይታወቅ የተፈቀደው አበል ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር የሰጠው ውሣኔ በጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ ተሽሮ እያለ የተጠራቀመው የቤት ኪራይ ይከፈል መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት አቤቱታው ለችሎቱ ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት ተጠሪዎች ቤታቸው በመወረሱ ምክንያት አበል እንዲከፈላቸው ክስ ለማቅረብ የቻሉት የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር አበሉ እንደከፈላቸው የሠጠውን ውሣኔ መሠረት አድርገው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር በአ/ቁ. 47/67 አንቀጽ 21/2/ መሠረት ትርፍ

ቤት የተወረሠበት ቤተሠብ ወይም ግለሠብ ከቤት ኪራይ በስተቀር ለመኖሪያ የሚሆን ሌላ ገቢ የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ በመሥራት ገቢ አስከሚያገኝ ድረስ በየወሩ ለመተዳደሪያ አበል እንዲከፈለው ሊወስን እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በዚህም መሠረት ህጉ የሠጠውን ስልጣን መሠረት አድርጐ የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር ለተጠሪዎች አበል እንደከፈላቸው ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ግን ይህ ውሳኔ በጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ የተሻረ መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ የተጠሪዎች ክርክር የስራና ከተማ ልማት ሚ/ር በአ/ቁ 47/67 የተሰጠውን ስልጣን መሠረት አድርጎ የሠጠውን ውሣኔ የጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ ለመሻር የሚያስችል ስልጣን የለውም የሚል ነው፡፡

ከመዝገቡ የጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ የሥራና ከተማ ልማት የሠጠውን ውሣኔ የሻረው በ29/12/87 እንደሆነ ተረድተናል፡፡ በዚህን ወቅት ደግሞ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት ከነሐሴ 15/1987 ጀምሮ ስራ ላይ ውሏል፡፡ በዚህ ህገ-መንግስት አንቀጽ 74/4/ ሁሉም ሚኒስቴሮች የሚገኙበትን የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደሚመራ፣ እንደሚያስተባብርና እንደሚወክል ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም ከነሐሴ 17/1987 ጀምሮ ስራ ላይ በነበረው የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አ/ቁ 4/87 አንቀጽ 11/1/ ሥር እያንዳንዱ ሚኒስትር፣ የሚመራውን ሚኒስቴር መ/ቤት የሚመለከቱ ሥራዎች ፐሮግራሞችና ህጎች አፈፃፀም ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስቴሮች ምክር ቤት መሆኑ ተገልጿል፡፡ ከነዚህ ህጎች አኳያ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚኒስቴር መ/ቤቶችን በበላይነት የመመራትና ስራቸውንም የመቆጣጠር ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቶቹ ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የፈፀሙትን ስህተት ማረምና ማስተካከል በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣን ስር የሚወድቅ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ለተጠሪዎች አበል እንዲከፈል የሠጠው ውሣኔ አግባብ ሆኖ ባለመገኘቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ውሣኔው መሻሩ ከስልጣኑ ውጪ ነው የሚያሠኝ አይሆንም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም በአ/ቁ 47/67 ሥር የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የሚሰጠውን ውሣኔ የጠቅላይ ሚኒስቴር ሊሽር፣ ሊያሻሽል ወይም ሊለውጥ የሚያስችለው ስልጣን በግልጽ አልተመለከተም በማለት ብቻ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ያለውን አጠቃላይ ስልጣን ከግንዛቤ ባለመክተት ውሣኔው የተሻረው ስልጣን በሌለው አካል ስለሆነ ውጤት የለውም ማለታቸው የህግ ስህተት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሆኑም ምንም እንኳን አበል ለተጠሪዎች እንዲከፈል ሥልጣን የነበረው አካል ወስኖ የነበረ ቢሆንም ይኸው ውሣኔ ሥልጣን ባለው የበላይ አካል የተሻረ በመሆኑ ተጠሪዎች አበል እንዲከፈላቸው የተሰጣቸውን መብት አጥተዋል፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቶቹ አበሉ እንዲከፈል መወሠናቸው የህግ ስህተት ነው፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 03721 በ27/05/95 እና በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 18942 በ8/8/96 የተሰጡት ውሣኔዎች ተሰሯል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
3. ከሥር ፍ/ቤት የመጣው መዝገብ ይመለስ፡፡

*መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡*



የሰ/መ/ቁ. 23339

መጋቢት 13 ቀን 1999 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አቶ ከማል በድሪ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ ጌታቸው ምህረቱ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

**አመልካች፡-** የኢት.ጉምሩክ ባለስልጣን

**ተጠሪ፡-** እነ አቶ አበሮ ኢርጋኖ

*የመንግሥት ሰራተኞች የስራ ክርክር - የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት ስልጣን - የጉምሩክ ሰራተኞችን አስተዳደር በተመለከተ የገቢዎች ሚኒስትር የሚያወጣው መመሪያ - አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 6/2/ለ*

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት የተጠሪዎቹን ክርክር ተቀብሎ ያስተናግድ ሲል የወሰነውን ውሣኔ በመቃወም የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>**ውሣኔ፡ -**</u> የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

የጉምሩክ ሰራተኞች የመንግሥት ሰራተኞች ቢሆኑም ከሌሎች የፌዴራል መ/ቤቶች ተለይተው የሚተዳደሩት የገቢዎች ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ እንጂ በፌዴራል መንግሥት ሰራተኞች አዋጅ ቁ. 262/1994 አይደለም፡፡